# የመንግሥት ወይም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ

የመንግሥት ወይም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ሕዝብን በማስተማር፣ በማሳወቅ እና በማዝናናት፣ የመንግሥት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና የልማት፣ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የሕዝቦችን አንድነት የሚያንፀባርቅ እና የብሔር ብሔረሰቦችንና የሕዝብን ቋንቋ፣ ባህላዊና ጥበባዊ እሴት የሚያስተዋውቅና የሚያጎለብት ፕሮግራም በማቅረብና በማስተማር የአገራችንን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት እና የሕዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ጉልህ ሚና የሚጫወት የብሮድካስት አገልግሎት በመሆኑ ይህን ሚናውን በተገቢው መንገድ እንዲጫወት ለማስቻል፤

የመንግሥት ወይም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ተደራሽነትን በማስፋት እና ውስን የሆነውን የሬዲዮና የቴሌቭዥን ሞገድ በአግባቡ እና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል በማስፈለጉ፣ እንዲሁም

ግልፅ እና ተጠያቂነት ያለው የመንግሥት ወይም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ ሥርአት መዘርጋት በማስፈለጉ በብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 533/1999 አንቀጽ 47 መሰረት ይህ መመሪያ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግሥት ወይም የሕዝብ ብሮድካስት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 1/2003" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ "የመንግሥት ወይም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት" ማለት ሕዝብን ለማስተማር፣ ለማሣወቅ እና ለማዝናናት በፌዴራል ወይም በክልል

መንግስት የሚቋቋም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመንግሥት በጀት የተመደበለት የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን አገልግሎት ነው፤

2/ "አመልካች" ማለት የመንግሥት ወይም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ እንዲሰጠው በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ቅፅ ሞልቶ ያመለከተ የፌዴራል ወይም የክልል መንግስት አካል ነው፤

3/ "ፕሮግራም" ማለት በድምጽ ወይም በምስል ወይም በሁለቱም ተቀነባብሮ ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት ወይም ሁለቱንም አካቶ የሚቀርብ የፕሮግራም ስርጭት ነው፤

4/ "ባለፈቃድ" ማለት በብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ወይም የብሮድካስት አገልግሎት አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሕጋዊ መንገድ የብሮድካስት አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለ የመንግሥት ወይም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

5/ "የመገናኛ ብዙሃን ማስፋፊያ የሥራ ሂደት" ማለት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብን ማመልከቻ ተቀብሎ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች መሟላታቸውን በማጣራት የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ በባለሥልጣኑ ውስጥ የተቋቋመ የሥራ ሂደት ነው።

6/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 47 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

7/ "አገር አቀፍ ስርጭት" ማለት ከአንድ ክልል በላይ የሚሸፍን ብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

8/ "ክልላዊ ስርጭት" ማለት ስርጭቱ በአንድ ክልል ብቻ የተወሰነ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፤

9/ "አገራዊ ፕሮግራም" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ በኢትዮጵያውያን የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው፤

10/ "የበላይ ኃላፊ" ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም እሱ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ነው፤

11/ "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ነው፤

12/ "ቦርድ" ማለት የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ቦርድ ነው፤

13/ "ሰው" ማለት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## ክፍል ሁለት

## ስለማመልከቻ እና ፈቃድ አሠጣጥ ሥነ ሥርዓት

### 3. ስለማመልከቻ ቅፅ

1/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች የያዘ የማመልከቻ ቅፅ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡-

ሀ) የአመልካቹ ወይም የጣቢያው መጠሪያ ስምና አድራሻ፣

ለ) የፕሮግራሙን አጠቃላይ ሁኔታ የሚገልፅ፣

ሐ) ለስርጭቱ የሚውለውን የመሣሪያ አይነትና ጉልበት፣

መ) ስርጭቱ የሚሸፍነው አካባቢ፣

ሠ) ለማቋቋም የተጠየቀው የሬዲዮ ሞገድ አይነት፣

ረ) የማሰራጫ መሳሪያ የሚተከልበትን ወይም የሚቋቋምበትን ቦታ እና ሌላ አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቅ መረጃ።

2/ አመልካቹ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል።

### 4. ከማመልከቻ ቅፅ ጋር ተያይዞ ስለሚቀርብ ሰነድ

አመልካቹ የሚከተሉትን ሰነዶች በማሟላት ከማመልከቻ ቅፁ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

1/ አመልካቹ የፌዴራሉ ወይም የክልሉ መንግሥት ምክር ቤት ባወጣው ሕግ መሰረት የተቋቋመ መሆኑን የሚያስረዳ ሰነድ፣

2/ የአመልካቹን የፋይናንስ፣ የሰው ሀይልና የቴክኒክ ሁኔታ የሚገልፅ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ እና ሌላ አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቅ መረጃ።

### 5. ስለፈቃድ መስፈርት

አመልካቹ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል።

1/ ተጠሪነቱ ለፌዴራሉ ወይም ለክልሉ መንግሥት ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መሆኑ፣

2/ አገልግሎቱን ለመስጠት ያለው የፋይናንስ እና የሰው ሀይል ብቃት፣

3/ በፕሮጀክት ጥናት ሰነድ የተዘረዘሩት መሳሪያዎች እና ቴክኖሎጂዎች አገልግሎቱን ለመስጠት የተመረጡ እና ብቃት ያላቸው መሆኑ፣

4/ በብሮድካሥት አገልግሎት አዋጅ አንቀፅ 23 መሰረት ፈቃድ የማይሰጠው ግለሰብ፣ በሕግ የሰውነት መብት ያልተሰጠው አካል፣ የፖለቲካ ድርጅት፣ የፖለቲካ ድርጅት ባለአክሲዮን የሆነበት ወይም የፖለቲካ ድርጅት የበላይ አመራር አባል ባለአክስዮን ወይም በማንኛውም ደረጃ የአመራር አባል የሆነበት ድርጅት፣ የሐይማኖት ድርጅት እና ሌላ ፈቃድ የማይሰጠው አካል በአመልካቹ ውስጥ የባለቤትነትም ሆነ የአክስዮን ድርሻ የሌለው መሆኑ።

## 6. የፈቃድ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

1/ የመንግሥት ወይም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚፈልግ አመልካች በማናቸውም ጊዜ ማመልከቻውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል።

2/ የመገናኛ ብዙሃን ማስፋፊያ የሥራ ሂደት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የቀረበለት ማመልከቻ በአንቀጽ 3፣ 4 እና 5 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟላ መሆኑን በማጣራት የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል።

3/ የበላይ ኃላፊው የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብና አስተያየት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል።

4/ የፈቃድ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች ለፈቃድ የተተመነውን ክፍያ ከፍሎ የፈቃድ ምስክር ወረቀት እንዲወስድ በፅሁፍ ይገለፅለታል።

5/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) በተገለፀው መሠረት ቀርቦ ክፍያውን ለፈፀመ እና ፈቃዱ በሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ስምምነት ሰነድ ለፈረመ አመልካች የፈቃድ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

6/ የፈቃድ ምስክር ወረቀት እንዲወስድ በጽሑፍ የተገለፀለት አመልካች ደብዳቤ በደረሰው በ2 ወር ጊዜ ውስጥ ክፍያ በመፈፀም እና በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ሰነድ በመፈረም የፈቃድ ምስክር ወረቀት ካልወሰደ የፈቃድ ውሣኔው ይሰረዛል።

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ቢኖርም ባለፈቃዱ የተዘጋጀውን ሰነድ በመፈረም የፈቃድ ምስክር ወረቀት ያልወሰደው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ ባለሥልጣኑ የ2 ወር ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድለት ይችላል።

## 7. የፈቃድ ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘ አመልካች

1/ ፈቃድ ያልተሰጠው አመልካች በበላይ ኃላፊው ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ14 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል።

2/ ቦርዱም የአመልካቹ አቤቱታ በደረሰው በ20 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

## 8. ባለፈቃዱ በማመልከቻው ስለገለፀው የፈቃድ ሁኔታ

1/ ባለፈቃዱ ፈቃዱን ለመውሰድ ባመለከተበት ወቅት በማመልከቻው ላይ የገለፀው የፈቃድ ሁኔታ የፈቃድ ግዴታ ሆኖ ይቀጥላል።

2/ ባለሥልጣኑ ባለፈቃዱ በማመልከቻው የገለፀውን የፈቃድ ሁኔታ እና ባለፈቃዱ ሊከተለው የሚገባ ግዴታን መሠረት ያደረገ የፈቃድ ስምምነት ሰነድ በማዘጋጀት ባለፈቃዱን ያስፈርማል።

## 9. የፈቃድ ዘመን

በብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ አንቀፅ 24 በተደነገገው መሰረት የመንግሥት ወይም የሕዝብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1/ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሠራጭ ሲሆን ለሬዲዮ 8 አመት ለቴሌቪዥን 10 አመት፤

2/ የሥርጭት ሽፋኑ በክልል ደረጃ የተወሰነ ሲሆን ለሬዲዮ 10 አመት ለቴሌቪዥን 12 አመት፤

3/ የስርጭት ሽፋኑ በአካባቢ ደረጃ የተወሰነ ሲሆን ለሬዲዮ 12 አመት ለቴሌቭዥን 14 አመት፤

4/ የሥርጭት ሽፋኑ በድሬዳዋ የተወሰነ ከሆነ ለሬዲዮ 10 አመት ለቴሌቪዥን 12 አመት፤

5/ የሥርጭት ሽፋኑ በአዲስ አበባ እና አካባቢዋ የተወሰነ ከሆነ ለሬዲዮ 6 አመት ለቴሌቪዥን 8 አመት ይሆናል።

## 10. ፈቃድ ስለማደስ

1/ ባለፈቃዱ የፈቃድ ጊዜ ገደብ ሳያልቅ ከ1 አመት ባልበለጠና ከ6 ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ማደሻ ቅፅ ሞልቶ የዕድሳት ማመልከቻውን ማቅረብ ይኖርበታል።

2/ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ከማደሱ በፊት፡-

ሀ) የሬዲዮ ሞገዱ ለሌላ ተግባር አለመፈለጉን፣

ለ) ባለፈቃዱ በተገልጋዩ ሕብረተሰብ ተቀባይነትን ያገኘና ተደጋጋሚ የሆነ የቅሬታ ሪከርድ የሌለበት መሆኑን፣

ሐ) በፈቃድ ዘመኑ ውስጥ በባለሥልጣኑ በተካሄደው የሞኒተሪንግ እና ክትትል ሥራ ባለፈቃዱ ተደጋጋሚ የጥፋት ሪከርድ ያልተገኘበት መሆኑን፣ እና

መ) ባለፈቃዱ በፈቃድ ዘመኑ ውስጥ አመታዊ ክፍያውን በወቅቱ ይከፍል የነበረ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

## ክፍል ሦስት

## ስለብሮድካስት አገልግሎት ክፍያ

## 11. ስለክፍያ በጠቅላላው

1/ ማንኛውም አመልካች የመመዝገቢያ ክፍያ ይከፍላል።

2/ ማንኛውም ባለፈቃድ የፈቃድ ክፍያ፣ አመታዊ ክፍያ እና የፈቃድ ማደሻ ክፍያ ይከፍላል።

3/ የክፍያው መጠን በባለሥልጣኑ በየጊዜው እየተጠና ይወሰናል።

## 12. ስለክፍያ ጊዜ

1/ አመልካቹ የማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ሲያቀርብ የመመዝገቢያ ክፍያ ይከፍላል።

2/ አመልካቹ የፈቃድ ምስክር ወረቀት ከመውሰዱ በፊት የፈቃድ ክፍያ ይከፍላል።

3/ ባለፈቃዱ ዓመታዊ ክፍያውን መክፈል የሚጀምረው የብሮድካስት አገልግሎት የሙከራ ስርጭት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

4/ ባለፈቃዱ የብሮድካስት አገልግሎት የሙከራ ስርጭት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ በየአመቱ አመታዊ ክፍያውን መክፈል ይኖርበታል።

5/ ባለፈቃዱ የብሮድካስት አገልግሎት የሙከራ ስርጭት ከጀመረበት ከማናቸውም ቀን ጀምሮ የተያዘው የመንግስት በጀት አመት በተጠናቀቀ በ60 ቀናት ውስጥ

የብሮድካስት አገልግሎት የሰጠበትን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ አመታዊ ክፍያውን ይከፍላል።

6/ ባለፈቃዱ የመንግስት በጀት አመት በተጠናቀቀ በ60 ቀናት ውስጥ አመታዊ ክፍያውን ካልከፈለ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር 5 በመቶ መቀጫ እየታከለበት ይከፍላል። ሆኖም የመቀጫው ጠቅላላ ድምር ከዋናው ክፍያ 50 በመቶ ሊበልጥ አይችልም።

## *ክፍል አራት*
## *ስለፈቃድ እገዳ፣ ስረዛ እና ቅሬታ አቀራረብ*

### 13. *ፈቃድ ስለማገድ*

1/ ባለፈቃዱ የአዋጁንና የዚህን መመሪያ ድንጋጌ ከጣሰ ፈቃዱ በባለሥልጣኑ ሊታገድ ይችላል።

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሚደረግ እገዳ በፅሑፍ ሆኖ እገዳው የተደረገበት ምክንያትና ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን ተገልፆ ለባለፈቃዱ እንዲደርሰው ይደረጋል።

3/ የዕግዱ ምክንያት በባለሥልጣኑ በተገለፀለት በ15 ቀናት ውስጥ ባለፈቃዱ የዕግዱን ምክንያት ካስወገደ ይህንኑ በፅሑፍ ማሳወቅ አለበት።

4/ የዕግዱ ምክንያት የተወገደ መሆኑን ባለሥልጣኑ ካረጋገጠ ዕግዱን ያነሳለታል።

### 14. *ፈቃድ ስለመሰረዝ*

1/ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊሰርዝ ይችላል፡-

ሀ) ባለፈቃዱ ፈቃድ ካወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ሥርጭቱን ያልጀመረ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) ባለፈቃዱ ፈቃዱን ያገኘው በተጭበረበረ ሰነድ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ) ጣቢያው ያለበቂ ምክንያት ሥርጭቱን ከአንድ ወር በላይ ሲያቋርጥ፣

መ) ጣቢያው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲዘጋ ሲወሰን፣

ሠ) ባለፈቃዱ በራሱ አነሳሽነት ሥራውን ሲያቆም፣

ረ) ባለፈቃዱ የሰው ልጆችን ስብዕናና ነፃነት ወይም ሥነ ምግባር የሚፃረር ወይም የሌሎችን እምነት የሚያንኳስስ፤ በመንግሥት ፀጥታ ወይም በሕገ መንግስቱ መሰረት በተቋቋመ የመንግሥት አስተዳደር ወይም በአገር መከላከያ ኃይል ላይ የወንጀል ድርጊት የሚፈፅም፤ የግለሰብን፣ የብሄር ብሄረሰብን፣ የሕዝብን ወይም የድርጅትን ስም የሚያጠፋ ወይም በሀሰት የሚወነጅል፤ ብሄርን ከብሄረሰብ የሚያጋጭ ወይም በሕዝቦች መካከል የእርስ በርስ ግጭት የሚያነሳሳ ወይም ጦርነት የሚቀሰቅስ ፕሮግራም አስተላልፎ ሲገኝ፣

ሰ) ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 11 እና 12 መሰረት ክፍያ ያልፈፀመ እንደሆነ እና

ሸ) ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ለፈቃድ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ካላስወገደ።

2/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ፈቃድ ሲሰርዝ ይህንኑ ለባለፈቃዱ በፅሑፍ ያሳውቃል።

3/ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ስርጭቱን ለመጀመር ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ያጋጠመው ስለመሆኑ ለባለሥልጣኑ ካስታወቀ እና የቀረበው ምክንያትም በባለሥልጣኑ ተቀባይነትን ካገኘ ስርጭቱን ለመጀመር የሚያስችል ከ6 ወር የማይበልጥ ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቀድለት ይችላል።

## 15. ቅሬታ ወይም አቤቱታ ስለማቅረብ

1/ ፈቃዱ የታገደበት ወይም የተሰረዘበት የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ፈቃዱ የታገደ ወይም የተሰረዘ ስለመሆኑ ውሳኔ በደረሰው በ14 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ወይም አቤቱታውን ለቦርዱ በፅሑፍ ሊያቀርብ ይችላል።

2/ ቦርዱም ቅሬታ ወይም አቤቱታ በቀረበለት በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

## 16. ስለማስፋፊያ ፈቃድ

1/ ማንኛውም ባለፈቃድ፡-

ሀ) ተጨማሪ ስርጭት ለማካሄድ ሲፈልግ፣

ለ) የጣቢያውን አቅም ለማሳደግ ሲፈልግ፣

ሐ) የቴክኖሎጂ ለውጥ ለማድረግ ሲፈልግ፣

መ) የማሰራጫ መሣሪያውን አቅም ከተፈቀደው መጠን በላይ ለማሳደግ ሲፈልግ፣

ሠ) በአንቴናው አይነትና ርዝመት ላይ ለውጥ ለማድረግ ሲፈልግ፣

ረ) የማሰራጫ አንቴናውን ቦታ መቀየር ሲፈልግ፣

ሰ) የአንቴና ምሰሶ ከፍታ ለመጨመር ሲፈልግ፣

ሸ) የውጭ ወይም የአገር ውስጥ ብሮድካስተር የሚያስተላልፈውን ፕሮግራም ተቀብሎ በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን ለማሰራጨት ሲፈልግ፣

ቀ) የስርጭት አገልግሎት ከሚሰጥበት አካባቢ ውጪ ሌሎች አካባቢዎችን ለማዳረስ አዲስ የሬዲዮ ሞገድ ሲፈልግ በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ የማስፋፊያ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

2/ የማስፋፊያ ፈቃድ የተሰጠው ባለፈቃድ የብሮድካስት አገልግ ሎቱን ለማስፋፋት ሲፈልግ መሳሪያው የሚተከልበትን ቦታ ከአስፈላጊ ዝርዝር መረጃ ጋር ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል።

3/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ቀ) መሰረት የማስፋፊያ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት፡-

ሀ) ፈቃድ በተጠየቀበት አካባቢ የተመዘገበ የሬዲዮ ሞገድ መኖሩን፣

ለ) የተመረጠው ማስፋፊያ ቦታ ከሌሎች የመገናኛ መሳሪያዎች ጋር ግጭት ወይም ጣልቃገብነትን የማይፈጥር መሆኑን፣

ሐ) የተመረጠው ማስፋፊያ ቦታ ለታቀደው አገልግሎት ብቁ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

4/ ባለሥልጣኑ ባለፈቃዱ ቀደም ብሎ ፈቃድ በወሰደበት የሬዲዮ ሞገድ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ፈቃድ ሲጠይቅ የብሮድካስት አገልግሎቱን ለማስፋፋት የቀረበው መሳሪያ፡-

ሀ) ከታቀደው የአገልግሎት ማስፋፊያ እቅድ ጋር መጣጣሙን እና

ለ) የመሳሪያው ጉልበት ሌላ የመገናኛ መሳሪያን አገልግሎት የማያውክ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

5/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ አንቀጽ 17 ከተዘረዘሩት የፈቃድ አይነቶች መካከል ቀደም ሲል ፈቃድ ካገኘበት የፈቃድ አይነት ውጪ ከባለሥልጣኑ ሌላ ተጨማሪ ፈቃድ ሳይሰጠው የብሮድካስት አገልግሎት መስጠት አይችልም።

## 17. ስለማሳወቅ

ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ለውጦች ሲያደርግ ለውጡን ባደረገ በ14 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) የማሰራጫ መሣሪያውን አቅም ከተፈቀደው መጠን በታች ሲቀንስ ፣

ለ) የፕሮግራምና የስርጭት ሰአት ለውጥ ሲያደርግ፣

ሐ) የአድራሻ ለውጥ ሲያደርግ፣

መ) የብሮድካስት ተቋሙን የበላይ ኃላፊ፣ የቦርድ አመራር አባላት እና የፕሮግራም ኃላፊ ለውጥ ሲያደርግ፣ እና

ሠ) በመሳሪያ ብልሽት ምክንያት የስርጭት አገልግሎቱን ለ1 ወር ሲያቋርጥ።

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌ

## 18. ጥቆማ እና ቅሬታን ስለማስተናገድ

1/ ባለፈቃዱ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥነ ሥርዓት በመዘርጋት ከሕብረተሰቡ የሚቀርብ ጥቆማ እና ቅሬታን ተቀብሎ ማስተናገድ ይኖርበታል።

2/ ባለፈቃዱ በየ6 ወሩ የ ጥቆማ እና ቅሬታ አቅራቢዎችን ስም፣ አድራሻ፣ የቀረቡለትን ጥቆማና ቅሬታዎች ብዛት፣ ምክንያት፣ ለጥቆማው ወይም ለቅሬታው የሰጠውን ምላሽና መሰል መረጃ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።

3/ ባለፈቃዱ ከሚሰጠው የብሮድካስት አገልግሎት ጋር በተያያዘ በማናቸውም ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት ከተወሰነበት የአቤቱታውን ብዛት፣ ምክንያት፣ የተሰጠውን ውሳኔና መሰል መረጃ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት።

## 19. *መመሪያውን ስለማሻሻል*

የባለሥልጣኑ ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል::

## 20. *መመሪያው የፀና ስለመሆኑ*

ይህ መመሪያ ከሰኔ 1 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

***የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ቦርድ***